## ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል
## 23 ኛ ሳምንት
## ነፍሴ የክርስቶስ ሙሽራ እንዴት ትሆናለች?

**የትምህርቱ ዓላማ**

- ደብረዘይትን የክርስቶስን ምጽኣት/ትርጉም ያለው ክብር ስለማክበር ማጥናት ትምህርቱ ተቀዳሚ ዓለማ ሲሆን፡፡
- ደብረዘይት ከሌሎች በዐላት ተለይቶ ወደፊት የሚደረገውን የምናስብበት ነው በዚህ በዓል ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት በጥልቀት የምናይበት መንፈሳዊ ሕይወታችንን ለክርስቶስ ሙሽራ ለመሆን የምናሳደግበትም ነው፡፡ ይህ እንዴት ይሆናል? እንማራለን........፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***"እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁ፡፡"*** 2ኛ ቆሮ.11÷2

**የሚተኮርባቸው ነጥቦች**

- የመንፈሳዊ በዓላት ትክክለኛ ትርጉም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅርና እኛም ለፍቅሩ የምንስጠው ምላሽ ነው፡፡
- በዚህም እርሱ በሕይወታችን ሁሉንም ነገር ይሆናል፡፡ ይመራናል፣በፍቃዱ እንጓዘለን... ለዚህም ነው ***አሙኑኤል*** - እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፡፡ ***አልፋና ኦሜጋ*** - ፊተኛውና ኃላኛው ብለን የምናምነው፡፡
- ታዲያ ይህ ከሆነ በእውነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በልባችን ውስጥ አለ? ይህ ከሆነ አንድም ኃጢአት አንፈጽምም፡፡የዓለም ፍቅርስ በጌታችን ፍቅር ተተክቶልናል ? ይህ ካልሆነ ሕይወታችንን አላስረከብነውም÷ምክንያቱም፡-

  ***" ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚችለው ማንም የለም ወይም አንዱን ይጠላል፡፡ ሁለተኛውንም ይወዳል÷ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል÷ወይም አንዱን ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ "ማቴ.*** 6÷24 ተብሎ ተጽፎልናል፡፡
- እግዚአብሔርን በሕይወታችን ሁሉ ለማግኘትና ከቅ. ጳውሎስም ጋር ***"እኔ አይደለሁም ክርስቶስ በእኔ ይኖራል እንጂ"*** በማለት÷ራሳችንን ከኃጢአት ማራቅ አለብን፡፡
- ሁለት ነገሮችን በማደረግም ከኃጢአት እንርቃለን፡-
  1. እግዚአብሔር እንዲጠብቀን መጸለይና ዲያብሎስ በማያገኝን የእግዚአብሔር አጥር መከለል፡፡የእግዚአብሔርንም ጥበቃ በእያንዳንዱ ጸሎታችን መጠየቅ፡፡
  2. ከኃጢአት ምክንያቶች በመራቅ በእግዚአብሔር ቃልና ቅዱስ ቁርባንን በተከታታይ በመቀበል ሥርየተ ኃጢአት በማግኘትም እንጠበቃለን፡፡
- ንስሐ ስንገባና ከኃጢአት ስንርቅም የክርስቶስ ሙሽራ እንሆናለን፡፡የክርስቶስ ሙሽራ መሆን ማለትም በዚህ ዓለምም ሆነ በገነት ከእርሱ ጋር መኖር ማለት ነው፡፡
- በዚህም እውነተኛ ክርስቲያን በዚህ ምድር ሰማያዊ ሕይወት ይኖረዋል፡፡ ይሄም ማለት ፍላጎቶቹ ከክርስቶስ ከመላእክት እና ቅዱሳን ጋር ይሆናል ማለት ነው፡፡ይሄን ሲያደርግም እለታዊ ሥራዎቹን በትጋት እያከናወነ ነው፡፡
- ለእግዚአብሔር ወይም ለሰይጣን መሆናችንን መለየት አለብን፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ከሆንና ከርሱም ጋር ከተባበርን እርሱ ንጉሳችን እኛም ሕዝቡ እንሆናለን፡፡ያኔም እኛ ሙሽሮቹ እርሱም ሙሽራችን ይሆናል ማለት ነው፡፡
- ነፍሳችን የክርስቶስ ሙሽራ ስትሆን ስንጠመቅ ያገኘነውን ንጽሕና፣ ልጅነትና ጸጋ ለመጠበቅና የምንችለውንና ከእኛ የሚጠበቀውንም እንፈጽማለን፡፡የዚህ ምሳሌም ራስ ወዳድነትን ሰብሮ የወጣ ፍቅር ነው፡፡ ለሰዎች ብርሃን ለመስጠት የሚቀልጠውን ሻማ አስታውሱ፡፡ እንዲሁም መልካ መዓዛውን ለማመንጨትና መልካም ሽታ ሆኖ በጌታ ፊት ለማረግ በማዕጠንት የሚቀልጠውን እጣንም አስቡ፡፡

**ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሙሽራይቱ ተናግሮአል**

- በማቴ. 25÷1-13 የተናገረው የ10ሩ ደናግል ምሳሌን ተመልከቱ፡፡5ቱ ልባሞች 5ቱ ሰነፎች ነበሩ፡፡ሁሉም ሙሽራውን ለመቀበል የፈለጉ ናቸው፡፡ 5ቱ ሰነፎች ግን በመብራታቸው ዘይት አልያዙም ነበር፡፡ ዘይቱ የፍቅር፣ የእምነትም ምሳሌ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡***"ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና"*** 1ኛ.ዮሐ.4÷7 የእግዚአብሔር ከሆንን ልባችን በፍቅር ሊሞላ ይገባል፡፡
- አንድ ቀን ደቀመዛሙርቱ ለምን እንደማይጾሙ ጌታችን ተጠየቀ ***"ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል በዚያን ጊዜም ይጦማሉ፡፡"*** ማቴ. 9÷15፡፡
- መጥምቁ ዮሐንስም ክርስቶስን ***"ሙሽ ራ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፡፡"*** ዮሐ.3÷29 ብሎ ሲገልጠው፡፡ባለራዕዩም***"ሙሽራይቱ ና ትላለች ብሏል፡፡"*** ***ስ***ለዚህም፡-

1. ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት ሁሌም መመርመርና ማስተዋል አለብን፡፡ ሙሽሪት ከሙሽራዋ ጋር የጠበቀ ፍቅርና አንድነት እንዳላት እኛም ከክርስቶስ ጋር ይህ አንድነት ሊኖረን ይገባል፡፡
2 .በፍቅር የተቃኘ ከክፉ ምኞት የተለየም ሕይወት ሊኖረን ይገባል፤ ፍቅርን በቁርጥ ውሳኔ ስንፈጽምና ስናከብር ራሳችንን ከእግዚአብሔር ቀጥተኛ እና እውነተኛ አንድነት ጋር እናገኘዋለን፡፡እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፡፡

<u>የክርስቶስ ሙሽራ</u>

- ***"እኔ የውዴ ነኝ እርሱም የእኔ ነው፡፡"***ክርስቶስ ከቤተክርስቲያን ጋር ያለው አንድነት በጥልቅ ፍቅር እና በፍጹም አንድነት የሚፈጸም ነው፡፡ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጠውም የሙሽራናሙሽሪት/ባልና ሚስት/ አንድነት ምሳሌ ነው፡፡
- ***"ክስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና፡፡"***
- ***"ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደሚወዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤"***
- ***"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡ ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፣ እኔ ግን ይህን ስለክርስቶና ስለ ቤተክርስቲያን አላለሁ፡፡"*** ኤፌ 5÷23-31
- በዚህ መንፈሳዊ አንድነት ቤተክርስቲያን ጌታዋንና ውድዋን በማኅልየ ማኅልይ ዘሰሎሞን ***"ውዴ የእኔ ነው÷እኔም የእርሱ ነኝ፤ በሱፍ አበባዎች መካልም መንጋውን ያሰማራል፡፡"*** መኃ 2÷16 ስትል፤
- እርሱም ***"መልካም እረኛ እኔ ነኝ፡፡መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል"*** ዮሐ.10÷11 ብሎል

<u>በተጨማሪም</u>፡-ለቤተክርስቲያን ሊፈርድላት በክፉዎችም ሊፈርድ ይመጣል፡፡ማቴ.25÷31-46 ***"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ÷ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡"***ራዕ.22÷12ብሏልና፡፡ይሄን በፍቅር የምትጠብቀው ሙሽሪይቱ ቤተክርስቲያንም ***"መንፈሱና ሙሽራይቱም ና ይላሉ፡፡"***ራዕ 22÷17 እንደተባለ በእምነትና በፍቅር ለክርስቶስ በመታዘዝም ትጠብቀዋለች፡፡

<u>ንጽሕትዋ ሙሽራ</u>

- ካለፈ ኃጢአት ራስዋን በማንጻትና በመቀደስ ወደ ሙሽራዋ የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር በአዲስ ሕይወት ትራመዳለች፡፡***"እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁ፡፡"*** 2ኛ ቆሮ.11÷2

- በዚህም ሰማያዊ ሙሽራን ለመቀበል እንደ ንጽሕት ድንግል የንጽሕናና የቅድስናን ሕይወት እንኖራለን፡፡ሰውነታችንንም ለእርሱ ቅዱስ እናደርጋለን፤በመልካም ምግባር በማስጌጥም ራሳችንን በክብር የሚመጣ ሙሽራን እንደምትቀበል ሙሽሪት እናዘጋጃለን፡፡

<u>የቤተክርስቲያን የሠርግ በዐል</u>

- ባለ ራዕዩ ቅዱስ ዮሐንስ ሰማያዊውን ደስታና ድል አድራጊዋን ቤተክርስቲያን ወደ ሙሽራዋ እንደምትሄድ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡፡ ***"ወደዚህና የበጉንም ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ አለኝ፡፡ በመንፈስም ወደ ታላቅና ወደረጅም ተራራ ወሰደኝ÷ የእግዚአብሔርም ክብር ያለባት ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ስትወርድ አሳየኝ..."*** *ራዕ.* 21÷9-10

- *ምዕመናን በተስፋቸው በክርስቶስ ጸንተው ሰማያዊቷን ሀገር የሚወርሱባት፤የጽድቅ ክብር፣የኃጢአትና የክፋት ውርደት የሚገለጥባት ቀን* የቤተክርስቲያን የሠርግ በዐል ቀን የምንላት እለት ምጽአት ናት፡፡ለዚህም ነው ቤተክስቲያን ይሄን እለት የምታሰበውና የምታከብረው፡፡ማቴ. 25÷31- ፍ/ም,*ራዕ*.21÷2-7,*ዕብ*.12÷22-24

<u>*ሙሽራይቱና አካሏ*</u>

- *ሙሽራይቱ ከባልዋ ጋር አንድ ስትሆን ሁለቱም አንድ ይሆናሉ፡፡ከዚያም ሁለት አይባሉም፡፡ ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ አካል ጋርም እንዲሁ ናት፡፡*
- *ይህ የማይከፋፈል አካል ነው፡፡ክርስቶስ ራስ ቤተክርስቲያን አካል ናቸው፡፡ ክርስቶስ በቤተክርስቲያን ይኖራል÷ መከራዎችዋም ሙከራው ነው* በርስዋ የሚሆነው በእርሱ እንደሆነ ነው፡፡ለዚህም ነው ቤተክርስትያንን ያሳድድ የነበረውን ሳውል ***"ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ"*** *ያለው* የሐዋ.*ሥ*.9÷

<u>*ሙሽራይቱና ቤተመቅደስዋ*</u>

- *ሙሽራይቱም ሙሉ ሕይወቷን ለባሏ ትሠጣለች፡፡ጌታም ያድርባታል፡፡*
- ቤተመቅደስ ለሌላ የማይሆን የጌታ ብቻ ማደሪያ ነው፡፡ ሙሽራይቱም ባሏን ስታገባ ሌላ በማግባት አትክደውምና፡፡ቤተክርስቲያንም የክርስቶስ እንጂ የክህደትና የኃጢአት ማደሪያ አትሆንም፡፡
- ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች ናቸው፡፡በሕይወታቸውም እግዚአብሔርን በምድር ሁሉ ፊት የሚያከብሩ ናቸው፡፡ ***"የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዘአብሔርን ቤተመቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና÷ያውም እናንተ ናችሁ፡፡"*** 1ኛ ቆሮ. 3÷16-17

**ይቆየን፡፡**